መመሪያ ቁጥር 1069/2017

የመንግስት መስሪያ ቤቶች ፈቃድ ከተሰጣቸው የክፍያ አገልግሎት ሰጪዎች ክፍያ መቀበል እንዲችሉ ለማድረግ የወጣ መመሪያ

# DIRECTIVE NO. 1069/2025

## A Directive on Mandatory Acceptance of Payments from all Licensed Payment Service Providers by Federal Public Bodies

ግንቦት 2017 ዓ.ም

**May/ 2025**



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

## መመሪያ ቁጥር 1069/2017

## የመንግስት መስሪያ ቤቶች ፈቃድ ከተሰጣቸው የክፍያ አገልግሎት ሰጪዎች ክፍያ መቀበል እንዲችሉ ለማድረግ የወጣ መመሪያ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፤ ፍትሃዊ ውድድርን የሚያበረታታ፤ ለሸማቾች ጥበቃን የሚሰጥ፤ የኤሌክትሮኒክ ገንዘብ ልውውጥን ደህንነት ማረጋገጥ የሚያስችል፤ ክፍያ ፈጻሚዎች የሚጠቀሙባቸው የኮምፒውተር ሲስተሞች ወይም ሶፍትዌሮች መረጃን መለዋወጥ እና በጋራ መጠቀም የሚችሉብትን የክፍያ ስርአት የሚፈቅድ እና ለክፍያ ሰነድ አውጪ ኩባንያዎች ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ የሚወስን መመሪያ ስራ ላይ ያዋለ በመሆኑ በመሆኑ፤

የመንግስት መስሪያ ቤቶች በዚህ መመሪያ መሰረት በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ፈቃድ ከተሰጣቸው የክፍያ ሰነድ አውጪ ድርጅቶች ክፍያ መቀበል የሚችሉበት መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የገንዘብ ሚኒስቴር በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 75 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል።

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የመንግስት መስርያ ቤቶች ፈቃድ ከተሰጣቸው የክፍያ አገልግሎት ሰጪዎች ክፍያ የሚቀበሉበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1069/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) "**የፋይናንስ ተቋም**" ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው ባንክ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋም፤የመድን ኩባንያ፤ የጠለፋ መድን ድርጅት፤ የክፍያ ሰነድ አውጪ፤ የክፍያ ስርአት አከናዋኝ፤ የሃዋላ ድርጅት፤ የፖስታ ቁጠባ፤ የውጭ ባንክ ወኪል፤የፖስታ ሃዋላ ተቋም ወይም ሌላ ተመሳሳይ ተቋም ነው።
2) "**የክፍያ አገልግሎት ሰጪ**" ማለት በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የክፍያ አፈጻጸምን ለመጀመር፤ለማጠናቀቅ ወይም የክፍያ ማስታረቅ ስራ ለመስራት የሚያገለግል አንድ ወይም ከአንድ በላይ የክፍያ ሰነዶችን እንዲያወጣ ፈቃድ የተሰጠው እንደ ንግድ ባንክ፤ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋም፤ ባንክ ያልሆነ የፋይናንስ ተቋም፤ የክፍያ ስርአት አከናዋኝ፤

## Directive No. 1069/2025

## A Directive on Mandatory Acceptance of Payments from all Licensed Payment Service Providers by Federal Public Bodies

WHEREAS, the Licensing and Authorization of Payment Instrument Issuer Directive of the National Bank of Ethiopia provide an enabling regulatory framework that promotes fair competition, ensures consumer protection and the integrity of electronic money transactions

WHEREAS, it has become necessary to give proper guidance to public bodies to accept payments from all Payment Instrument Issuers licensed by the National bank of Ethiopia under said Directive;

NOW, THEREFORE, the Ministry of Finance in accordance with the power vested in it under Article 75 of the Federal Government Financial Administration Proclamation hereby issues the following Directive.

### 1. Short Title

This Directive may be cited as "A Directive on Acceptance of Payments from all Licensed Payment Service Providers by Federal Public Bodies No. 1069/2025"

### 2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this Directive:

1) "**Financial Institution**" means a bank, microfinance institution, an insurance company, a re-insurer, a payment instrument issuer, a payment system operator, a money transfer institution. a postal saving, representative office of a foreign bank, a postal money transfer institution or such other similar institution as determined and licensed by the National Bank of Ethiopia.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

አውቶማቲክ የመክፈያ መሳሪያ አከናዋኝ ያለ ድርጅት ነው።

3) **"ክፍያ"** ማለት የመንግስት መስሪያ ቤት ለሚያቀርበው እቃ፣ ለሚሰጠው አገልግሎት፣ በህግ ለተወሰነ ክፍያ፣ ለታክስ፣ ቅጣት፣ ድጎማ፣ ስጦታ ወይም ለኢትዮጵያ መንግስት የሚፈጸም ሌላ ማናቸውም ግዴታ፣ ኃላፊነት ወይም መብት በከፋዩ አማካኝነት ለመንግስት መስሪያ ቤት ገንዘብ ማስተላለፍ ወይም መላክ ነው።

4) **"የክፍያ መፈጸሚያ ስርአት"** ማለት የቴክኖሎጂ መድረክን ወይም አገልግሎትን በመጠቀም በዴቢት ካርድ፣ በክሬዲት ካርድ እና በሌሎችም የዲጂታል ክፍያ ዘዴዎች ኦንላይን የሚፈጸሙ ክፍያዎችን ለማዘዝ የሚያስችል ስርአት ነው።

5) **"አስቀድሞ ክፍያ የተፈጸበት ሰነድ"** ማለት አስቀድሞ የተከፈለ የተወሰነ የገንዘብ ዋጋ እንዲኖረው ተደርጎ የተዘጋጀ በጥሬ ገንዘብ፣ በዴቢት/ክሬዲት ካርድ ምትክ የሚያገለግል የገንዘብ ዝውውርን ጨምሮ የእቃ እና የገልግሎት ግዥን ለመፈጸም የሚውል የፋይናንስ ሰነድ ነው።

6) **"የመንግስት መስሪያ ቤት"** ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በፌዴራል መንግስት በጀት የሚተዳደር መስሪያ ቤት ነው።

7) **"አዋጅ"** ማለት የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 (እንደተሻሻለ) ነው።

8) በዚህ መመሪያ ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ቃላት እና ሃረጎች በአዋጁ የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል።

2) **"Payment Service Provider"** means any person or entity that is duly licensed or authorized by the National Bank of Ethiopia to issue one or more instruments or devices used for the initiation, routing or settlement of payments such as commercial banks, Microfinance institutes, Non-bank financial institutions, Payment system operators, Automatic Teller Machine Operators.

3) "**Payment**" means an act of transferring or remitting funds by a payer to a Public Body in exchange for a good, service, fee, charge, tax, penalty, interest, subsidy, grant or any other financial obligation, liability or entitlement of the Government of Ethiopia;

4) "**Payment Gateway"** means a technology platform or service that authorize and process online payments, typically for credit cards, debit cards and other forms of digital payment.

5) "**Prepaid Payment Instrument**" means a financial instrument issued with a specific monetary value already preloaded and can be used in lieu of cash or credit/debit card to facilitate the purchase of goods and services, including funds transfers.

6) **"Public Body"** means any organ of the Federal Government which is partly or wholly financed by Government allocated budget;

7) "**Proclamation**" means the Federal Government Financial Administration Proclamation No. 648/2009 (as amended).

8) Words and Terms used in this Directive but not defined herein shall have the definitions ascribed to them in the Proclamation.

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት በሚቀበሉት ማናቸውም ክፍያ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 3. Scope of Application

This Directive shall apply to all payments received by Public Bodies in accordance with the provisions of the Federal Government Financial Administration Proclamation.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

## 4. አላማ

የዚህ መመሪያ አላማ ሁሉን አሳታፊ የሆነ፤ አማራጭ የክፍያ ዘዴን ስራ ላይ የሚያውል፤ በፋይናንስ ስራ አሳታፊነትን የሚያረጋግጥ፤ በውድድር ላይ የተመሰረተ የዲጂታል ክፍያ ስርአት እንዲኖር ማድረግ ነው።

## 5. በተፈቀዱ የክፍያ ሰነዶች ክፍያን ስለመቀበል

የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጨምሮ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጣቸው ድርጅቶች በሚያወጧቸው የክፍያ ሰነዶች ክፍያ መቀበል አለባቸው፡-

1) በዴቢት ካርድ/ በክሬዲት ካርድ፤
2) አስቀድሞ ክፍያ የተፈጸመበት ሰነድ፤
3) የሞባይል ገንዘብ መክፈያ፤
4) የሞባይል እና የኢንተርኔት ባንክ፤
5) በብሄራዊ የክፍያ ስርአት አዋጅ ቁጥር 718/2003 (እንደተሻሻለው) በተደነገገው መሰረት በተፈቀደላቸው የፋይናንስ ድርጅቶች የሚፈጸም የገንዘብ ዝውውር፤

## 6. ከክፍያ ስርአቶች ጋር ማጣጣም

የክፍያ አገልግሎት ከሚሰጡ ከሁሉም ድርጅቶች ክፍያ መቀበል እንዲቻል የመንግስት መስሪያ ቤቶች የክፍያ መቀበያ ስርአታቸውን ፈቃድ ከተሰጣቸው አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እና ከክፍያ መፈጸሚያ ስርአቶች ጋር ማጣጣም አለባቸው።

## 7. አድልዎ የሌለበት አጠቃቀም

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ በተሰጠው የክፍያ ሰነድ አውጪ የተዘጋጀ እና ህጋዊ ስርአትን ያሟላ እስከሆነ ድረስ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የክፍያ ሰነዱን ያወጣውን ድርጅት ማንነት ምክንያት በማድረግ ህጋዊ የክፍያ ሰነድን ላለመቀበል ወይም ገደብ እንዲደረግበት ለማድረግ አይችሉም።

## 8. ወጪ

የክፍያ ሰነዱ ምርጫ እና ክፍያው ጋር የተያያዘው ወጪ ከግምት ውስጥ ሳይገባ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በመንግስት የተወሰነውን ሙሉ ክፍያ መቀበል አለባቸው።

## 4. Objectives

The objectives of this Directive are enhancing open access, payment alternatives, financial inclusion and competitive digital payments.

## 5. Acceptance of Licensed Payment Instruments

All Public Bodies shall be required to accept payments through any payment instrument issued by entities licensed and regulated by the National Bank of Ethiopia; including but not limited to:

1) Debit cards/ Credit Cards
2) Prepaid payment instruments (PPIs);
3) Mobile wallets;
4) Mobile and internet banking;
5) Fund transfers as described in the National Payment Systems Proclamation No 718/2011; from any licensed Financial Institution.

## 6. Integration with Systems

All Public Bodies are mandated to ensure the integration of their payment collection systems with authorized payment gateways and service providers to facilitate receipt of payments from all Payment Service Providers.

## 7. Non- Discriminatory Access

Public Bodies shall not deny or restrict acceptance of any legitimate payment instrument solely on the basis of the Payment Instrument Issuer, provided such issuer is duly licensed by the National Bank of Ethiopia and compliant with regulatory norms.

## 8. Costs

Irrespective of the choice of the instrument and the associated transaction costs, the public bodies shall receive the full amount set by the Government.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

## 9. ስራ ላይ የሚውልበት ጊዜ

1) የመንግስት መስሪያ ቤቶች አስፈላጊውን የቴክኒክ እና የአስተዳደር ስርአት በማሟላት ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ90 ቀናት ጊዜ ውስጥ ማሟላት አለባቸው።
2) ወደሙሉ ተግባር እስከሚገባበት ጊዜ ድረስ አፈጻጸሙ የሚገኝበትን ደረጃ የሚያሳይ የከንውን ሪፖርት በየ30 ቀኑ ልዩነት ለገንዘብ ሚኒስቴር መላክ አለበት።

## 9. Timeline for Implementation

1) All Public Bodies shall complete all necessary technical and administrative arrangements within 90 days from the date of issuance of this Directive.
2) Progress reports shall be submitted to the Ministry of Finance with 30-day intervals following the issuance of this directive, until full compliance is achieved.

## 10. ክትትል እና ትግበራ

የገንዘብ ሚኒስቴር የኢንስፔክሽን መምሪያ ይህ መመሪያ በትክክል ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን የመከታተል እና እንስፔክት የማድረግ ሃላፊነት ያለበት ሲሆን፤ በመመሪያው መሰረት ተፈጻሚ መደረጉን ለማረጋገጥ መረጃ ለመጠየቅ ይችላል።

## 10. Monitoring and Compliance

The Inspection Department of the Ministry of Finance shall oversee implementation and may carry out inspections or request data to verify adherence.

## 11. ማብራሪያ እና ድጋፍ ስለመጠየቅ

የመንግስት መስሪያ ቤቶች በአተገባበር ረገድ ሊከተሉት ስለሚገባው አሰራር ማብራሪያ ወይም የቴክኒክ ድጋፍ ለማግኘት ሲፈልጉ የገንዘብ ሚኒስቴር ትሬዠሪ መምሪያን ለመጠየቅ ይችላሉ።

## 11. Clarifications and Support

Public Bodies may contact the Treasury Department of the Ministry of Finance for any operational guidance or technical assistance.

## 12. የኤሌክትሮኒክ የክፍያ ስርአት መመሪያ ተፈጻሚነት

የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚፈጽሙትን ክፍያ በሚመለከት የፌዴራል መንግስት የኢሌክትሮኒክ የክፍያ ስርአት መመሪያ ቁጥር 71/2013 ተፈጻሚነት የሚቀጥል ይሆናል።

## 12. Applicability of the Electronic Payment Directive

The Federal Government Electronic Payment Directive No 71/2020 shall continue to be applicable on payments to be made by Public Bodies.

## 13. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማናቸውም መመሪያ በዚህ መመሪያ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

## 13. Non- Applicability

No directives or practices inconsistent with this Directive shall have effect with respect to matters provided in this Directive.

## 14. ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በገንዘብ ሚኒስቴር ይፋዊ ድህረ ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት 18 ቀን 2017 አ.ም

አህመድ ሺዴ

## 14. Effective Date

This Directive shall come into force on the date of its publication on the Ministry of Finance's official website following its registration with the Ministry of Justice.

Addis Ababa 26th May, 2025

Ahmed Shide



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

| | |
|---|---|
| ሚኒስትር | Minister of Finance |



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.